# አብሮነት

እንረስ ካላችሁ በሰላም እንረስ
የናንተው አዳራሽ የኛም ጎጆ ሳይፈርስ፡፡
እንኑር ካላችሁ እንኑር በሰላም እንኑር በጤና
ለናንተም ደህንነት ለኛም ህልውና
መሆኑን አውቃችሁ ተከዜ ድንበሩ
እንኑር በአብሮነት እንደ አባት አደሩ።
እንኑር ካላችሁ ህዝባችን ተዋዶ
ዘረኛው ሥርዓት ተስሩ ተንዶ
በመሃከላችን ዕርቀ-ሰላም ወርዶ
ማንም ከማን ሳያንስ ሁሉም በዕኩልነት
እንኑር ካላችሁ እንኑር በአብሮነት።
እንደግ ካላችሁ አብረን ዕንበልፅግ
መዝረፍ አቁማችሁ ተገዙና በህግ
በገበያ ውድድር ሰቶ በመቀበል
ነግዶ በማትረፍ አብረን ከፍ እንበል።
እንኑር ካላችሁ እንኑር በጤና
የዴሞክራሲን መብት አክብሩና
በችሎታና ዕውቀት መስፈርት ተመዝነን
ባንድ ሰው አንድ ድምፅ ምርጫ ተወዳድረን
በሰበሰብነው ድምጽ እንደ ክህሎታችን
የስልጣን ባለቤት እናርገው ህዝባችን።
ሆኖም ግን ከዚህ ውጭ ከሆነ ምርጫችሁ
ወረተኛው ጊዜ ነገ ሲከዳችሁ
በብረቱ ትግል ማን ፈሪ ማን ጀግና
አበጣሪው ሰፌድ ጊዜ ይሆንና
ጨለማው ዐይን ወግቶ ሲረዝም ሌሊቱ
ሰማዩ ሲጠቁር ሲቀላ መሬቱ
ኋላ እንዳይከፋችሁ ሲጀመር እልቂቱ።

መስከረም 2009
አብርሃም በየነ